OFFICE OF THE STATE
SUPERINTENDENT OF EDUCATION

ውድ ወላጅ ወይም አሳዳጊ፣

በጸደይ 2023፣ የእርስዎ ልጅ በስቴት-ደረጃ የሚሰጠውን የእንግሊዝኛ ቋንቋ አርት/ የማንበብ እና የመጻፍ ችሎታ (እንግልሽ ላንጓጅ አርትስ) (ELA) እና/ወይም ሂሳብ ወስዷል/ወስዳለች። የእኛ አመታዊ ምዘናዎች ለተማሪዎቻችን በጣም አስፈላጊ የሆኑ እውቀት እና ክህሎቶችን ይለካሉ – ክህሎቶች እንደ መጻፍ፣ ችግር መፍታት፣ እና ሌሎች በሂሳብ እና ELA መተማመን እና ስኬትን የሚያመጡ መሰረታዊ ክህሎቶች።

የኮሮናቫይረስ (ኮቪድ-19) ወረርሽኝ በመማር ማስተማር እና በተማሪዎች መማር ላይ ተፅእኖ ያደረጉ ተግዳሮቶችን እንዳመጣ እናውቃለን። እንደ ወረዳ፣ የዘንድሮው ዓመት የምዘና ውጤቶ ካለፈው አመት ጋር ሲነጻጸር መሻሻል መኖሩን አሳይተዋል፣ ይህም በየእለቱ በት/ቤቶች እየተካሄደ ያለውን ጠንካራ ስራ ያሳያል። የስቴት አቀፍ ምዘና ውጤቶች በዲስትሪክቱ ዙሪያ ያለውን የተማሪ አፈጻጸም ለመመልከት ጠቃሚ የመረጃ ምንጭ ሆነው ይቀጥላሉ፣ እና ተማሪዎቻቸውን እና አስተማሪዎቻቸውን እንዴት በተሻለ ሁኔታ መደገፍ እንደሚችሉ የት/ቤቶችን ውሳኔ ለማሳወቅ ይጠቅማል።

ልጅዎ ላጠናቀቀው እያንዳንዱ ምዘና ከልጅዎ ትምህርት ቤት የውጤት ሪፖርት ያገኛሉ። ይህ መመሪያ ከልጅዎ የውጤት ዘገባ ሊማሯቸው ወደሚችሏቸው ጠቃሚ የግንዛቤ ነጥቦች በመምራት ልጅዎ በቀጣዩ አመት እንዲሻሻል ለመርዳትም ግብዓቶችን ይሰጥዎታል። የልጅዎ የውጤት ሪፖርቶች ካልደረሱዎት፣ እባክዎ ልጅዎ በ2022-23 የተማረበትን/ችበትን ትምህርት ቤት ያነጋግሩ እና ለቅጂው
ይጠይቁ።

የልጅዎ የELA እና የሂሳብ ምዘናዎች ውጤት ልጅዎ በደምብ እየሰራ ያለውን እና ተጨማሪ እርዳታ የሚያስፈልገውን ለማሳየት ተከፋፍሏል። አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የልጅዎ አስተማሪዎች ተጨማሪ ድጋፍ ወይም የበለጠ ፈታኝ ስራ ለማቅረብ ይህንን መረጃ ሊጠቀሙበት ይችላሉ። በተጨማሪ እርስዎ ይህን መረጃ በቤት ውስጥ የመማር ጊዜን ለማተኮር ሊጠቀሙበት ይችላሉ።

የምዘና ውጤቶች የልጅዎን አጠቃላይ የትምህርት ታሪክ እንደማይናገሩ እናውቃለን። ውጤቶቹ ከብዙ መለኪያዎች ውስጥ አንዱ ነው – የሪፖርት ካርድ ውጤት፣ የክፍል አፈጻጸም፣ እና የአስተማሪ ግብረመልስን የሚያካትት – ሁሉም ባንድ ላይ ልጅዎ በትምህርት ቤት ውስጥ ያለውን እድገት ምስል የሚፈጥሩ። በዚያ ምስል ውስጥ፣ አመታዊ ምዘናዎቹ እርስዎ እና የልጅዎ አስተማሪዎች የእርስዎ ልጅ ባለፈው አመት ለELA እና ሂሳብ የመንግስት የይዘት መስፈርቶች ልጅዎ ያሳየውን እድገት በተሻለ ሁኔታ እንዲረዱ የተሰሩ ናቸው።
ምዘናዎች የሁሉንም ተማሪዎች ፍላጎት ለመደገፍ ትምህርት ቤቶች ምን አይነት ግብዓቶች እንደሚያስፈልጋቸው በተሻለ ለመረዳት እንድንችልም ይረዱናል።

በመጨረሻም፣ ግባችን ተማሪዎች በት/ቤት ስኬታማ እንዲሆኑ እና ህልሞቻቸውን እና ምኞቶቻቸውን ለመከተል ዝግጁ መሆናቸውን ማረጋገጥ ነው። አጠቃላይ ጥያቄዎች ካለዎት ወይም ስለምዘናዎች የበለጠ መረጃ ከፈለጉ፣ እባክዎ የእኛን ድህረገጽ ይጎብኙ በ osse.dc.gov/parcc ወይም ከልጅዎ አስተማሪ ጋር ይወያዩ። በተጨማሪ በዚህ መምሪያ ገጽ 4 ላይ ያሉትን ግብአቶች መጠቀም ይችላሉ።

በስቴት ትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ ቢሮ (OSSE)፣ ሁሉም ተማሪዎች በከፍተኛ ደረጃ መማር እና ስኬት ላይ መድረስ እንደሚችሉ እናውቃለን፣ በተጨማሪም ልጅዎ ስኬት ላይ እንዲደርስ/እንድትደርስ ከእርስዎ ጋር አብረን የመስራት እድሉን እናደንቃለን።


እናመሰግናለን፣

ዶ/ር Christina Grant
የDC ግዛት የትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ

1050 First Street NE, Washington, DC 20002
(202) 727-6436 TTY: 711 | osse.dc.gov

# የውጤት ሪፖርቱን መከፋፈል፥ የፊት ለፊት

ይህ መመሪያ ከልጅዎ የውጤት ሪፖርት ሊማሯቸው ወደሚችሏቸው በጣም አስፈላጊ የግንዛቤ ነጥቦች ይመራዎታል። እንዲሁም ልጅዎ በሚመጣው አመት አፈፃፀሙን እንዲያሻሽል ለመርዳት አጋዥ ግብዓቶችን ይሰጥዎታል።




## 1) የምዘና መግለጫ

በዘገባው አናት ላይ የምዘናው አጭር መግለጫ አለ። ስለዚህ ዘገባ ማንኛውም አይነት ጥያቄ ካለዎት በአንቀፁ ግርጌ ላይ የአድራሻ መረጃ አለ።

## 2) ልጅዎ በአጠቃላይ አፈፃፀሙ እንዴት ነበረ?


የልጅዎ ውጤት ከአምስቱ የአፈጻጸም ደረጃዎች አንዱ ላይ ያርፋል። የአፈጻጸም ደረጃዎቹ ልጅዎ ለክፍሉ ደረጃ የሚጠበቅበትን/የሚጠበቅባትን ማሟላቱን/ማሟላቷን ይለያል። ደረጃ 4 ወይም 5 ውጤት ማለት ልጅዎ በዚያ የትምህርት አይነት የሚጠበቅበትን አሟልቷል ወይም ከሚጠበቅበት በላይ ሰርቷል ማለት ነው። በተጨማሪም ለቀጣይ የክፍል ደረጃ መስመር ላይ ናቸው ማለት ነው።

ከደረጃ 4 በታች ውጤት ያላቸው ተማሪዎች አሁንም የክፍሉን ደረጃ ክህሎቶችን እና እውቀት እያዳበሩ ሊሆን ይችላል።

## የውጤት ዘገባው ሲብራራ፡- ይመለሱ

### 3) ልጅዎ ምን ያህል የተለየ እውቀት እና ችሎታ ተማረ?

ተማሪዎች በተለያዩ ክፍሎች ስለ ጥንካሬዎቻቸው እና ተጨማሪ ድጋፍ የሚፈልጉባቸው ቁልፍ ዘርፎችን በተመለከተ የበለጠ ዝርዝር መረጃ ያገኛሉ። ይሄ ክፍል ልጅዎ ለእያንዳንዱ ቁልፍ የምዘና ክፍል የሚጠበቅባቸውን ካሟሉ ወይ ከዛ በላይ ካለፉ፣ ወደ የሚጠበቅባቸው ከቀረቡ፣ ወይ በከፊል የሚጠበቅባቸውን ካሟሉ ተማሪዎች እኩል አፈፃፀም ይኑረው ወይ አይኑረው ያሳያል።



የ7ተኛ ክፍል የሂሳብ ዝርዝሮች

የአፈፃፀም ደረጃ ደረጃ 4

ስኮት በምዘናው ቁልፍ ቦታዎች ላይ እንዴት ሰራ?

በአጠቃላይ በዚህ ምዘና 4ኛ ደረጃ ላይ የሰሩ ተማሪዎች የሚጠበቁባቸውን ትምህርታዊ ነገሮች አሟልተው ለቀጣዩ ክፍል ወይም ኮርስ ዝግጁ ሊሆኑ ይችላሉ። ይህ ክፍል ልጅዎ ለእያንዳንዱ ቁልፍ የምዘና ክፍል የሚጠበቅባቸውን ካሟሉ ወይ ከዛ በላይ ካለፉ፣ ወደ የሚጠበቅባቸው ከቀረቡ፣ ወይ እስካሁን የሚጠበቅባቸውን ካላሟሉ ወይ በከፊል ካሟሉ ተማሪዎች እኩል አፈፃፀም ይኑረው አይኑረው ያሳያል።

| ዋና ይዘት | ተጨማሪ እና የድጋፍ ይዘት | የሂሳብ-ነክ ምክንያታዊነትን መግለጽ | ሞዴሊንግ እና ተግባራዊነት |
|---|---|---|---|
| መመጣጠኖች፣ ቁጥሮች፣ አልጀብራ ላይ መስራት | ዙሪያ፣ ስፋት፣ ራሽናል ይዘት፣ ስታቲስቲክስ፣ ፕሮባብሊቲ (የመከሰት እድል) | መፍትሄዎችን ማረጋገጥ እና መሳሪያዎችን በመጠቀም | የሌሎች ጥያቄዎችን ምልከቶችን እና የምክንያታዊነት መወከል እና መፍታት |
| ያሟላል ወይም ✓ | ያሟላል ወይም ✓ | ወደማማሟላቱ ● | ወደማማሟላቱ ● |

✓ የሚጠበቅበትን አሟልቷል ወይም አልፏል የሚጠበቅበትን ለማሟላት ተቃርቧል ከተጠበቀው በታች ነው

የስኮት አፈፃፀም እንዴት ይነፃፀራል?

ስኮት የ 7ተኛ ክፍል የሂሳብ ፈተናን ከወሰዱ በAnywhere Middle School (የኤኒዌር መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት) ያሉ 71% ከሚሆኑት ተማሪዎች የተሻለ ውጤት — 71%

ስኮት የ 7ተኛ ክፍል የሂሳብ ፈተናን ከወሰዱ በኮሎምቢያ ዲስትሪክት የህዝብ ትምህርት ቤቶች ያሉ 66% ከሚሆኑት ተማሪዎች የተሻለ ውጤት አስመዝግቧል። — 66%

ስኮት የ 7ተኛ ክፍል የሂሳብ ፈተናን ከወሰዱ በዲሲ ውስጥ ያሉ 75% ከሚሆኑት ተማሪዎች የተሻለ ውጤት አስመዝግቧል። — 75%



ቀጥሎ ምን አለ?

ይህንን ዘገባ ከተማሪዎ መምህር ጋር ወደ ቀጣዩ ጉባኤዎ ያምጡት። የስኮት መምህራንን መጠየቅ ይችላሉ፥

- በዚህ ዓመት በሂሳብ ስኮት ምን እየተማረ ነው? ስኮት
- እንዴት እየሆነ ነው?
- በዚህ ዓመት ከስኮት ጋር አብሬ ለመስራት እንዴት ይሄን መረጃ እጠቀማለሁ?
- ስኮትን ለመደገፍ ምን አይነት ግብዓቶችን መጠቀም አለብኝ?

ተጨማሪ መረጃ ከየት ማግኘት ይችላሉ?

- የስኮት ትምህርት ቤት እና ሌሎች ትምህርት ቤቶች እንዴት ውጤት እንዳስመዘገቡ፥ ይጎብኙ www.OSSE.dc.gov/parcc፣ ወይም ለOSSE በ(202) 719-6500 ላይ ይደውሉ
- ፈተናው እንዴት እንደተዘጋጀ እና ምን እንደሚመዝን፣ ይጎብኙ www.OSSE.dc.gov/parcc፣ ወይም ለOSSE በ(202) 719-6500 ላይ ይደውሉ
- እነዚህን ሪፖርቶች ቤተሰቦች፣ አስተማሪዎች፣ እና ትምህርት ቤቶች ይጠቀማሉ፣ ይጎብኙ www.OSSE.dc.gov/parcc፣ ወይም ለOSSE በ(202) 719-6500 ላይ ይደውሉ

### 4) ልጅዎ ከሌሎች ተማሪዎች ጋር ሲወዳደሩ እንዴት አይነት አፈፃፀም አሳይተዋል?

ይህ ሪፖርት በትምህርት ቤት ደረጃ፣ የአካባቢ ትምህርት ኤጀንሲ ደረጃ፣ እና በዲስትሪክቱ ውስጥ የልጅዎ አፈጻጸም ከእኩዮቻቸው ጋር እንዴት እንደሚነጻጸር ያሳያል።

### 5) ቀጥሎ ምን አለ?

በውጤት ዘገባ ውስጥ ያለው መረጃ የተማሪን አፈፃፀም ለመለካት እና ለክህሎት ግንባታ መመሪያ ለመስጠት የተዘጋጀ ነው። ይህ ክፍል የልጅዎን አስተማሪ ስለ አፈፃፀሙ ሊጠይቋቸው የሚችሏቸውን ጥቂት ጥያቄዎችን ያቀርባል። ተጨማሪ መረጃ የት ማግኘት እንደሚችሉም ያካፍላል።

# ግብዓቶች እና ድጋፍ

ከታች ያሉት ልጅዎ በELA እና ሂሳብ እንዲያድግ/እንድታድግ የሚረዱ ጠቃሚ ግብአቶችን፣ እንዲሁም ውጤቱን ከልጅዎ እና ከልጅዎ አስተማሪ ጋር የሚወያዩበት በርካታ ጠቃሚ ምክሮች ናቸው።

## ስለየDC PARCC ውጤቶች ወይም ስለ PARCC ምዘና የበለጠ ማወቅ ይፈልጋሉ?

ስለ PARCC ምዘናዎች እና የኮመን ኮር የስቴት ደረጃዎች የበለጠ መረጃ ለማግኘት የሚከተሉትን ድህረገጾች ይጎብኙ፥

- OSSE.dc.gov/parcc ምዘናዎች፣ ውጤቶች እና ግብአቶች ላይ መረጃ ለማግኘት
- Results.OSSE.dc.gov የተማሪዎ ትምህርት ቤት እና በ DC ውስጥ ያሉ ሌሎች ትምህርት ቤቶች እንዴት እንደፈጸሙ መረጃ ለማግኘት።
- PARCConline.org ለወላጆች እና ተማሪዎች ስለ ምዘናዎች እና ግብአቶች መረጃ ለማግኘት።
- DC.mypearsonsupport.com/practice-tests/ ከክፍል 3 እስከ 11 ላሉ ተማሪዎች የመለማመጃ ፈተናዎች እና ሞዴል ጥያቄዎችን ያቀርባል።
- CoreStandards.org ስለ ታወቁ ዋና የመንግስት መለኪያዎች ለመማር።

## አሁን የልጅዎ የፈተና ውጤቶች ስላሎት፣ ቀጣዩስ ምንድን ነው?

እነዚህን ምዘናዎች በመጠቀም ልጅዎ በአካዳሚክ እንዲያሻሽል እንዲረዳው የሚያስችሉ የተለያዩ ግብአቶች አሉ። እነዚህ ግብአቶች ተማሪዎችን እና ቤተሰቦችን የመርዳት ብቸኛ ዓላማ ያላቸው ኢጋዥ መሳሪያዎች እንዲሆኑ የታሰቡ ናቸው። OSSE እና ዲስትሪክቱ እንዚህን የመሰሉ የትኛውም ዓይነት ግብአቶች አይደግፉም እና/ወይም ስፖንሰር አያደርጉም እና እነዚህ መረጃ ሰጪ ምክሮች እንዲሆኑ የታሰቡ ናቸው፥

- GreatSchools.org በቤት ውስጥ ከልጅዎ ጋር ትምህርቶችን እና መልመጃዎችን መስራት እንዲችሉ የይዘት እና ክፍሉን የሚመጥን ቪዲዮዎች ገጽታ አለው።
- BeALearningHero.org ለወላጆች ክህሎቶችን ጨምሮ ሰፊ የግብዓቶች ሀብት አለው።
- የገንቢ ገጽ እና የመማሪያ መሳሪያዎች ገጽ፣ ዲሲ'ን መሰረት ላደረገ ክፍል፣ የትምህርት ዓይነት እና የይዘት ዙሪያ ግብዓቶችን ይበጃል።

## ከልጅዎ ጋር ስለ ውጤቱ ለመነጋገር ይፈልጋሉ?

እንክብካቤ ሰጪዎች ከልጆቻቸው ጋር መነጋገር ላይ ባለሙያዎች ናቸው። ስለልጅዎ የፈተና ውጤት ሲናገሩ ማስታወስ ያለብዎት ጥቂት ጠቃሚ ነገሮች ከዚህ በታች አሉ፡-

- የፈተና ውጤቶች አንድ የአፈፃፀም መለኪያ ብቻ ናቸው።
- ጥንካሬዎች ላይ አተኩሩ።
- የዕድገት ቦታዎችን (ለምሳሌ፣ የኦንላይን ላይ ልምምድ፣ ከአስተማሪ ጋር መስራት) ለመፍታት ስልቶችን ተወያዩ።

## ከልጅዎ አስተማሪ ጋር ስለ ውጤቱ ለመነጋገር ይፈልጋሉ?

ከልጅዎ አስተማሪ ጋር ውይይትን ለመምራት የሚረዱ ጥቂት ጥያቄዎች ከዚህ በታች አሉ፡-

- በዚህ አመት የልጄ የሂሳብ የመማር ግቦች ምንድን ናቸው? በንባብ?
- ልጄ በሂሳብ ክፍል አፈጻጸሙ እንዴት ነው? በእንግሊዘኛ ቋንቋ አርትስ?
- ልጄ እነዚህን ግቦች ለማሳካት በትምህርት ቤት እና በቤት ውስጥ የሚያስፈልገው ተጨማሪ ድጋፍ ምንድን ነው?
- በእርስዎ ምልከታ ላይ በመመስረት፣ ልጄ በደምብ የሚሰራው ምንድን ነው? ለልጄ አንዳንድ የእድገት ዘርፎች ምንድን ናቸው?